# አርበኞች ግንቦት 7 ን የምትደግፉ ንገሩን!
# በዘንድሮ ግንቦት 20 ግን ምን ታስቧል

ሰርፀ ደስታ

May 16, 2018

ዛሬ ለካ ግንቦት 7 ነው፡፡ አርበኞች ግንቦት 7 ምን ይሚሉት ሥም ነው አሁን? ለነገሩ እኔ ምን አገባኝ ከፈለጉ ግንቦት 20ም ይበሉት? ብቻ ይሄ ግንቦት ውስጥ ቀን የሚቆጥሩብን ቡድኖች እኔን አይመቹኝም ብቻ ሳይሆን በቃ ምን ልበላችሁ….፡፡ የሆነ ሆኖ ዘንድሮ ግንቦት ለመሰሪዎች የተመቸ አይመስልም፡፡ ግን እስኪ እንደው ይሄ ራሱን ግንቦት 7 ነኝ ስለሚለው ቡድን አንድ እንኳን የሚነግረን ጠፉ? ማለቴ እውነቱን? አርበኛ ነኝ ሲልስ ትንሽ እንኳን አይሰቀጥጠውም? ደጋፊዎቹስ ምን አይተው ይሆን የሚደግፉት? መደገፍ እኮ አይነት አለው ደግሞ፡፡ ኸረ አልገባኝም እባካችሁ እስኪ ስለግንቦት 7 ስለሚባለው ንገሩን ከአላችሁ አለቀላችሁ የስድብ ናዳ ይወርድባችኋል፡፡ እኔ ስድቡ ይቀርልኝ እንደሁ ብዬ ትንሽ ያከብሩኛል ከምላቸው ደጋፊዎችም ሞከርኩ ያው ነው ከስድብ ያልተናነሰ ነው መልሳቸው፡፡ አመክንዮ(ሎጂክ) የሌለውን ነገር እንዴት ሰው ተቀብሎ ደጋፊ ይሆናል፡፡ ኸረ ረጋ በሉ፡፡ እኔ እስከማየው ግንቦት 7 የተባለ ቡድን በሻቢያ በኩል ነጻ አወጣለሁ እያለ ለዓመታት ሕዝብን ሲዎሽ የኖረ፣ በሥሙ ሕዝብ አሸባሪ እየተባለ እንዲገደል ሥሙን ለወያኔ ያከራየ፣ የአርበኝነትን ዋጋ ያረከሰ፣ በከተማና በየአገሩ እየዞሩ ገንዘብ እየለቀሙ በሕዝብ የሚነግድ፣ ከሻቢያ ጀምሮ ከኢትዮጵያ ቀንደኛ ጠላቶች ጋር የሚሰራ የወያኔ ሕቡዕ ቡድን ነው የሚል እሳቤ ነው ያለኝ፡፡

ከዚህ በተጨማሪ የአቶ አንዳርጋቸው ጽጌ መያዝ ሚስጢር የዚሁ ቡድን ልዩ ሴራዊ ድራማ ነው የሚል ከፍተኛ ጥርጣሬ ነው ያለኝ፡፡ ቡድኑ እንደ ሌላው ሕዝብ የሆነ ሰሞን አብሮ ሆይ ሆይ አለ እንጂ ስለ አንዳርጋቸው ክትትልም የሚያደርግ አይመስልም፡፡ አሁን በርካታ ታሳሪዎች ሲለቀቁ ሕዝብ ስለ አንዳርጋቸው መናገር ጀመረ እንጂ ቡድኑ ምን እንዳለ አልሰማሁም፡፡ ዛሬ ደግሞ ክሱ ተነሳ ሲባል ቅድሚያ የደስታና የምስጋና መግለጫ ያወጣል ሲባል ምንም ሲል አልሰማሁም፡፡ ነው እኔ ስለግንቦት 7 ብዙም ስለማልከታተል፡፡ ምን ግን እኮ ሳልፈልገው ነው በደጋፊዎቹ በኩል የሚደርሰኝ፡፡ የአንዳርጋቸው ይለቀቃል ማለት ግን ጭራሽ አስኮርፎት እንዳይሆን፡፡ ከወያኔ ጋር በሕቡዕ እየሰራ ከሆነ ባያስኮርፈው ነው የሚገርመው፡፡ የወያኔ ወሮበሎችን ይሄው እየዘረርናቸው ነው፡፡ ወሮ በላ በሙሉ እየታደነ ይዘረራል፡፡ ወያኔዎቹስ ፊትለፊት ስለተሳተፉ ይቀልላቸዋል፡፡ ጉዱ በሕቡዕ ሲሰሩ የኖሩት በተለይ ሕዝብ ተሸውዶም ይሆን ከሴራቸው ጋር ተባብሮ ሲያጨበጭብላቸው የነበሩ ሚስጢራቸው አደባባይ ሲወጣ ነው፡፡ ለመሆኑ ያ ደምህት የተባለው ወያኔና ሻቢያ ያስታጠቁት ቡድን ምን እየሰራ ነው? አባይ ጸሐዬ ሰሞኑን መከላከያውን እኮ መቀሌ አምጥተንዋል አለ አሉ፡፡ ለነገሩ አሉ ብሎ ማውራት አልወድም፡፡ ሰውዬው ይህን አለ አላለ ግን እንድህ ማለትን ከማያፍሩ እንደሆነ እናውቀዋለን፡፡ የትግራይ ትግሬ ግን ንቃ አሁን፡፡ ነጻነትህን ጠይቅ ሌሎች ራሳቸውን ነጻ እድርገው ነጻ ላልወጡ እየታገሉ ነው፡፡ የሶማሌ ሕዝብ ጥሩ ይዟል፡፡ የወሮበሎቹ ቀንደኛ ታማኞች እነ አብዲ ኢሌና የአንዳንድ ክልሎች ለምሳሌ የቤኒሻንጉል ቡሙዝ ባለስልጣናት ዛሬም አልነቁም፡፡ እንደፈርዖን ወይም እንደ ኖሕ ዘመን ሰዎች ማዕበሉ መጥቶ እየጠራረጋቸውም የወያኔ ቡድን ታማኝነታቸው እንዳያስተውሉ ጋርዷቸዋል፡፡

ለነገሩ ዛሬ ግንቦት 7 ነው ስለግ 7 ብጠይቅ ይሻለኛል፡፡ ሰሞኑን ደግሞ አይኔ ነው ወይስ ትክክል ነው ለአንዴና ለመጨረሻ ጊዜ

ሕዝባዊ ትግሉን ከፍጻሜ ለማድረስ ምናምን የሚል ቅስቀሳ ይሄው ግ 7 ሲያደርግ ሰማሁ ልበል? ቀልደኛ ነው፡፡ እስከዛሬ የት ነበር፡፡ ዛሬ ትግሉ ከሚፈለገው ፍጥነት በላይ የሕዝብን የበላይነት እያረጋገጠ በመጣበት ወቅት ትግል አጋጥናለሁ ብሎ ለማውራት ቀዳሚ የሆነው፡፡ ከዚህ በኋላ ማንኛውንም ሴራዊ አካሂደ በመለሳለስ የምናልፈው የለም፡፡ ግንቦት 7 ወያኔን እየወደቀ መሆኑ እርግጠኛ ሲሆን ነው ዛሬ በኢትዮጵያ ሕዝብ ትግል ሥም አፋጥናለሁ የሚለው፡፡ በዚህ ሂደትም በፍጥነት ሥም በማሳከር የወያኔን ሕልውና ለማስቀጠል፡፡ አንድም አሁን እየሄድንበት ከአለው ፍጥነት በላይ ፍጥነት አንፈልግም፡፡ ይልቁንስ ግብዣ ቀርቦለት የለ ለምን ተቃዋሚ ከሆነ አገር ቤት ለመግባት ጥረት አልሞከረም፡፡ ሴራው ግልጽና ግልጽ ነው፡፡ በአሁኑ ወቅት የአለውን ሂደት ወደአልተፈለገ አቅጣጫ ለማስቀየር ነው፡፡ ኢትዮጵያዊ የሆንክ ሁሉ የእስከዛሬውን የግንቦት 7 አካሂዶች ሁሉ አጢን፡፡ ከቅንጅት ጀምሮ ነገሮች እንዴት ወደማይሆን አቅጣጫ ሲመሩ እንደነበር አስተውል፡፡ አንዲት ሴት ብርቱካን ሚደቅሳ ከማን ጋር እንደሆነች ሳታውቅ ብዙ የተጎዳች መሠለኝ፡፡ ሌሎቹ የዛ ቅንጅት የተባለው ቡድን ግለሰቦች ድራማ ሲጫወቱ እንደነበር አሁን ነው ነገሩ የሚገባን፡፡ አስተውሉ፡፡

ሥለዚህ ኢትዮጵያውያን ሁሉ አሁን እየሆነ ያለውን የለውጥ ሂደት በአትኩሮት እንድትከታተሉትና ወደፊት ለማስኬድ ከአዲሱ ጠ/ሚኒስቴርና አጋሮቹ (በተለይ የኦሮሚያና አማራ አመራሮች) ጋር ወደፊት መቀጠል አለብን፡፡ ጠ/ሚኒስቴሩ ከሚናገረው ነገር ያፈነገጠ ሥራ ሲሰራ ከተገኘም እንዲታረም እንነግረዋለን፡፡ በአለማወቅ ሊሳሳት የሚችልባቸው ጉዳዮች ስላሉ፡፡ እኛ (ሕዝብ) የምንለውን እንዲሰማ እኛም በምንችለው ሁሉ እንድንደግፈው ግድ ይላል፡፡ በዚህ ወቅት ትግል አፋጥናለሁ፣ አሁን እየተፈጠረ ያለውን የአገሪቱን መንግስታዊ አሰራር አዳክማለሁ ብሎ የተነሳ ሁሉ የወያኔ ደጋፊ እንጂ የሕዝብ እንዳይመስላችሁ፡፡ ወያኔ እየተንኮታኮተች ስለመጣች ነው ይሄ ሁሉ መንፈራገጥ፡፡ ሕዝብ ያንን ሁሉ ስቃይ ሲደርስበት ሲያሾፉ የነበሩ ቡድኖች ዛሬ ላይ ዋና የትግል አራማጅ መሆናቸው የሴራውን ጥልቀት እንድታይ ነው ይሄን ጥቆማ የምሰጠው፡፡

በመጨረሻ ለጠ/ሚኒስቴር አብይና አጋሮቹ(ገዱ-ለማ ቡድን) ከሁሉ በፊት የኢትዮጵያ መንግስታዊ መዋቅር ላይ አስቡ፡፡ የ 27 ዓመቱን የቡድናዊ(የኢሕአዴግ) መዋቅር ሙሉ በሙሉ ፈርሶ የኢትዮጵያ መንግስት ሊመሠረት ይገባል፡፡ ኢትዮጵያ ያለ መንግስት 27 ዓመት ኖራለች፡፡ ምን ማለትህ ነው አትበሉ፡፡ መከላከያው የኢሕዴግ እንጂ የኢትዮጵያ አደልም፣ ቤተመንግስቱ እንደዛው፣ ፍትሁ እንደዛው፣ በአጠቃለይ በኢትዮጵያ የሆነው መንግስታዊ መዋቅርን ሙሉ በሙሉ በአንድ ቡድን መዋቅር መተካት ነበር፡፡ ቢያንስ መከላከያው እንኳን መንግስታዊ ቢሆን ሕዝብ ይህ ሁሉ ግፍ ሲደርስበት በግፍ አድራሾቹ ላይ እርምጃ ይወስድ ነበር፡፡ ሆኖም መከላከያው የወሮበላው ወያኔ/ኢሕአዴግ ቅጥር እንጂ የሕዝብ በአለመሆኑ ሕዝብ ፍትሀዊ ጥያቄ ሲያቀርብ ሊድልና ሊያሰቃይ ከካምፕ ወደከተማ ነው የመጣው፡፡ በአጠቃለይ የወያኔ/ኢሕአዴግ ቡድን ጠባቂ እንጂ የኢትዮጵያ መከላከያ አልነበረም፡፡ ከአጼ ሚኒሊክ ጀምሮ የነበረው የኢትዮጵያ መከላከያ ሙሉ በሙሉ መዋቅሩ ፈርሶ ነው የወያኔ/ኢሕአዴግ ጠባቂዎች የተቀጠሩት፡፡ በደርግ ጊዜ የነበረው የመከላከያ ሰራዊት ከሀይለስላሴ ነው የመጣው፡፡ በወያኔ ግን እንዲህ አደለም፡፡ ለዛም ነበር ያለ እፍረት እንዳለ የትግሬ አዛዦች ሙሉ በሙሉ የተቆጣጠሩት፡፡ በቃ የሆነው የግል ካምፓኒያቸው ነው ያደረጉት፡፡ ሌሎች መንግስታዊ ተቋማትም እንዳልነበሩ ሆነው ፈርሰው የወያኔው ቡድን ጉዳይ አስፈጻሚ ሆነዋል፡፡ ሌላ ቀርቶ ታሪካዊው የኢትዮጵያ አየር መንገድ፡፡ አየር መንገዱ ግን ለኢትዮጵ ታማኝነቱን በአስገራሚ ሁኔታ አስቀርቷል፡፡ ዛሬም ድረስ ብቸኛው የኢትዮጵያን ባንዲራ (የመለስ ኮከብ የለሌበትን) በጭራው ላይ ለዓለም እያውለበለበ የሚጓዝ ኢትዮጵያዊ ተቋም ነው፡፡ አንበሳውንም እናነሳለን ብለው በአንድ ወቅት ሲንፈራገጡ ነበር፡፡ ዛሬም አንበሳው ከፊት ባንዲራው ከኋላ በኢትዮጵያ አየር መንገድ አውሮፕላኖች ላይ አሉ፡፡ ከዚህ በኋላ ማንም አይነካቸው፡፡ ባንዲራችንም በኢትዮጵያ ምድር ሁሉ ተመልሶ ይውለበለባል፡፡ የኦከቡን ምልክት ማጥፋት ከሕገመንግስታዊው ሴራ መንቀሎች ውስጥ አንዱ

ይሆናል፡፡ አብይም ለማም፣ ገዱም ሌሎችም ይህን እያሰባችሁ ቀጥሉ፡፡

ለአብይ አሁንም የወሮበሎቹን የሽብር አዋጅ(አስቸኳዩን ማለቴ ነው ለካ ብዙ የሽብር አዋጆች ናቸው የታወጁብን) በፍጥነት አንሳ፡፡ በተግባር እየሰራ እንዳልሆነ እናውቃለን ግን በይፋ መነሳቱን ለሕዝብ ማወጅ አለብህ፡፡ ከዚህ በፊትም እንዲሁ ታውጆ መነሳቱ ግን ሳይነገር ቀጥሏል፡፡ እንዲህ ያለ የወንበዴ አሰራር የለም፡፡ ፓርላማህን ጥራና እሱንም ሌሎችንም አዋጆች በአንዴ አስወግድ፡፡ ሁለት ሶስት ጉባዔም አያስፈልግህም፡፡ ቀጥሎ ሕገመንግስት የተባለውን የወንበዴው ቡድን ሰነድን እንዳለ ተዋግዶ አዲስ እንዲዘጋጅ፡፡ ለጥቆማ ኃ/ሥላሴ በሥልጣናቸው መጨረሻ አዘጋጅተውት ለአዋጅ የቀረው ሕገመንግስት አለ ሲባል ሰምቼአለሁ፡፡ ይዘቱ ኢትዮጵያን የሚወክል እንደሆነ ይነገርለታል፡፡ ሌላ ቀርቶ ከአማርኛ በተጨማሪ ይሄ ተብሎ ባይጠቀስም አንድ ሌላ ቋንቋ ማዕላዊው መንግስት የሥራ ቋንቋ እንዲሆን ይደነግጋል ተብሏል፡፡ እንደሚባለው ያ ሰነድ ብዙ ጥሩ ነገሮች ተካተውበታል፡፡ ሙሉ በሙሉ በዛን ዘመን ያለውን መቅዳት ባይቻል ጥሩ ከሆነ ጥሩ መሠረት ይሆናል የሚል እምነት አለኝ፡፡ የወያኔው መለስን ድርሳን በምንም መስፈርት በኢትዮጵያ ህገመንግስት ለግብዓት የሚሆን የለውም፡፡ ብዙዎች ሕገ መንግስቱ ጥሩ ነው የአፈጻጸም ችግር ነው ያለበት እያሉ ሲያሞካሹት ሰምቻለሁ፡፡ ሳያነቡት ከሆነ እንጂ ሕገ መንግስቱ ከመጀመሪያ እስከመጨረሻ የወያኔን ሴራ ለማስፈጸም ታስቦ ቃላቶቹ የተሰነጉት፡፡ የክልሎቹን ሕገመንግስት ስናይ ደግሞ የባሰ ነገር እናያለን፡፡ ለመሳሌ ምዕራፍ ሁለት አንቀጽ 8 ወይም 9 የኦሮሚያን እንውሰድና የክልሉ የሥልጣን ባለቤት የኦሮሞ ሕዝብ ነው ይላል፡፡ የሱማሌም እንደዛው፡፡ በቃ ዜጎች ከክልላቸው ውጭ በሌሎች ክልል መኖር እነዳይችሉ በግልጽ  የደነገገ ሕግመንግስት ተብሎ የተቀመጠ ሰነድ ነው፡፡ ከኦሮሞ ውጭ ያለ ሌላ ሕዝብ በኦሮምያ ስልጣን የለውም፡፡ በሶማሌ ክልል ኦሮሞ ስልጣን የለውም፡፡ ይህ ማለት ሲተረጎም መምረጥም መመረጥም አይችልም፣ ለመኖርም ሶማሌ ከአልፈቀደለት ኦሮሞ በሶማሌ መኖር አይችልም እንደማለት ነው፡፡ እንዲህ ያለ ሰነድ በሕገመንግስትነት በተቀመጠባት አገር እንዴት የዜጎችን መብት ማስጠበቅ ይቻላል? በአጠቃላይ ማንነትን መሠረት ያደረገ መንግስትም ፓርቲም ለወደፊቱ እንዲወገድ መሠራት አለበት፡፡ ኦሕዴድ የኦሮሞ እንጂ በኦሮሚያ ውስጥ የሚኖሩ ሕዝቦች አይደለም፡፡ ሶደፓም እንደዛው፡፡ ብዓዴን ከነጭርሱ ሥሙንም ያወጡለት ትግሬዎች ናቸው ተብሏልና በአማራ ክልል የትግሬዎች ሊሆን ይችላል ግን ሥያሜው አሁንም አማራ ብቻ ነው፡፡ ሌላ ቀርቶ በአገሪቱ ታላቅ ታሪክ ያለውን የአገውን ሕዝብ አንኳን ያካተተ ሥያሜ የለውም፡፡ የባለሥልጣናቱም አስተሳሰብ ይሄው ነው፡፡ የኦሮምያ ፕሬዘዳንት የኦሮሞ ፕሬዘደንት ሳይሆን የክልሉ ነው፡፡ የአማራም እንደዛው፡፡ አሁን በአለው አመለካከት ግን እንዲህ አደለም የሚታሰበው፡፡ በነገራችን ላይ ከክልል ሕገ መንግስታት ብቸኛው ስልጣን በክልሉ የሚኖሩ ሕዝቦች ነው በሚል የጠቀሰው የአማራው ክልል ሕገ-መንግስት ብቻ ሳይሆን አይቀርም፡፡ በአጠቃላይ እንደነዚህ ያሉ ሰነዶች ከእነፈጠሩት የአመለካከት ነቀርሳ መወገድ አለባቸው፡፡

በመጨረሻም ለጠ/ሚኒስቴር አብይ ግንቦት 20ን የተዋረድንበት ቀን ለአለፉት 27 ሕይወታቸውን በግፍ ያጡትን ወገኖቻችንን አስበን የምንውልብ ቀን ሆኖ እንዲታወስልን፡፡ ኢትዮጵያዊነትና ኢትዮጵያውያን የተዋረዱበት ቀን፡፡ የኢትዮጵያ መንግስታዊ መዋቅር ፈርሶ የወንበዴዎች መዋቀር በአገሪቱ የነገሰበት ቀን፡፡

ልዑል እግዚአብሔር ኢትዮጵያንና ሕዝቦቿን ይባርክ! አሜን!

ሰርፀ ደስታ